| | |
|---|---|
| ተዛማጅ ሠነዶች፡- | ABC, ABC-RA, IOD-RA |
| ኃላፊነት የሚመለከተው ጽ/ቤት: | የትምህርት ቤቶች ምክትል ሱፐር ኢንተንደንት<br>Deputy Superintendent of Schools፤<br>የስርአተ ትምህርትና የትምህርት ፕሮግራሞች ቢሮ<br>Office of Curriculum and Instructional Programs |

## ጀማሪ የብዝሃ ቋንቋ ተማሪዎች ትምህርት

### A. ዓላማ

በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ውስጥ እያደገ የመጣ የመድብለ ቋንቋ ተማሪዎችን ትምህርት በእሴት ላይ የተመሰረተ ማዕቀፍ ለማብጀት

እያደገ የመጣ የብዝሃ ቋንቋ ተማሪዎችን ትምህርት በተመለከተ የፌደራል እና የስቴት ህጎችና መመሪያዎች መከበራቸውን ለማረጋገጥ

### B. ጉዳዩ

በቤታቸው ውስጥ ከእንግሊዘኛ ውጭ ሌላ ቋንቋ እየተጠቀሙ ያሉ ልጆች በትምህርት ቤት ሁለት ቋንቋ ተናጋሪ ወይም መድብለ ቋንቋ ተማሪ የመሆን እድል አላቸው። የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ዲፓርትመንት (MSDE) እነዚህን ተማሪዎች በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ውስጥ ከሚማሩት እንግሊዘኛ በተጨማሪ ቢያንስ አንድ ሌላ ቋንቋ በተመሳሳይ ጊዜ እንደሚማሩ እውቅና በመስጠት እያደገ የመጣ የመድብለ ቋንቋ ተማሪዎች ይላቸዋል። MSDE መድብለ ቋንቋ ተናጋሪነትን እንደ እሴት በመቁጠር እውቅና ይሰጣል፣ እንዲሁም በእሴት ላይ የተመሰረተ አመለካከትን ያበረታታል፤ ይህም እያደገ በመጣው የመድብለ ቋንቋ ተማሪዎች ጥንካሬዎች ላይ የሚያተኩር እና የሀሳብ፣ የባህል እና የባህርይ ልዩነትን በሜሪላንድ ላሉ ትምህርት ቤቶች እንደ አወንታዊ እሴቶች አድርጎ ይመለከታቸዋል።

የፌደራል እና የስቴት ህግ እያደገ የመጣው የመድብለ ቋንቋ ተማሪዎች የሚያጋጥሟቸውን ተግዳሮቶች መቋቋም እንዲያስችላቸው እና እንደዚህ አይነት ተማሪዎች በትምህርት ፕሮግራሞች ላይ ሙሉ በሙሉ እንዳይሳተፉ

የሚያግዷቸውን መሰናክሎች ለማስወገድ የትምህርት ፕሮግራሞች ድጋፍ እንዲሰጣቸው ይደነግጋሉ። እንደነዚህ ያሉ ፕሮግራሞች እና አገልግሎቶች ወላጆች/አሳዳጊዎች በእነርሱ ምትክ ውጤታማ በሆነ መንገድ እንዲያቀነቅኑላቸው ለመርዳት የመድብለ ቋንቋ ግምገማዎችን፣ የካውንስሊንግ አገልግሎትን፣ እና የወላጅ/አሳዳጊ ግንኙነትና ተደራሽነትን ያካትታሉ።

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) እያደገ የመጣ የብዝሃ ቋንቋ ተማሪዎች በርካታ አገሮችን እና ቋንቋዎችን የሚወክሉ፣ ከሁሉም ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃዎች የመጡ እና የተለያየ የትምህርት እና የልምድ ዳራ ያላቸው የተማሪዎች ቡድን ናቸው። የሞንትጎመሪ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ ABC፣ የቤተሰብ እና የትምህርት ቤት አጋርነት፣የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ትምህርት ቤቶችና ማህበረሰቦች ሁሉም በተለያዩ ወንች፣ ማንነቶች፣ ልምዶች፣እና ባህሎች የበለፀጉ መሆናቸውን ያረጋግጣል።

C. አቋም

1. የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ እያደገ ለመጣው የመድብለ ቋንቋ ተማሪዎች ያለውን ቁርጠኝነት እንደሚከተለው ያረጋግጣል፦

    a) የመድብለ ቋንቋ ተናጋሪ ተማሪዎችን ከሁሉም ተማሪዎች የሚጠበቀውን አይነት ተመሳሳይ ከፍተኛ የትምህርት ውጤታማነት እንደሚጠበቅባቸው ማረጋገጥ፤

    b) ከሁሉም ተማሪዎች ከሚጠበቀው ብቃት ጋር በሚጣጣም መልኩ የመድብለ ቋንቋ ተናጋሪ ተማሪዎች በአካዳሚክስ እና በግለሰብ ደረጃ የእንግሊዝኛ ቋንቋን በማዳመጥ፣ በመናገር፣ በማንበብ እና በመፃፍ ከፍተኛ ችሎታዎችን እንዲያዳብሩ ለውጤታማነት የሚያግዛቸው እድሎችን መስጠት።

    c) ከሁሉም ተማሪዎች የሚጠበቀውን የንባብ እና የቋንቋ ስነጥበብ፣ ሂሳብ፣ ሶሻል ስተዲስ/ማህበራዊ ጥናት፣ ሳይንስ፣ የሙያ እና የቴክኖሎጂ ትምህርት፣ ኪነ ጥበብ፣ ጤና እና የአካል ማጎልመሻ ትምህርትን ጨምሮ በሁሉም የትምህርት ዘርፎች MSDE የሚጠበቅባቸውን ጠንካራ የአፈጻጸም ደረጃዎች ማሟላት ወይም ማለፍ፣

d) ቀደም ብሎ ለተማሩት ትምህርታቸው፣ የግንዛቤ ችሎታ፣ ወይም ልዩ ፍላጎቶች፣ እና የእንግሊዝኛ ቋንቋ የብቃት ደረጃቸውን የሚያንፀባርቅ ተገቢውን ትምህርት ለመድብለ ቋንቋ ተማሪዎች ማቅረብ።

e) የመድብለ ቋንቋ ተማሪዎችን ከፌዴራል፣ ከስቴት እና ከአከባቢ ደረጃዎች ጋር የተጣጣሙ ተገቢ እና ትክክለኛ ግምገማዎችን ምዘና መስጠት እና የእንግሊዝኛ ቋንቋ ብቃታቸውን ግምት ውስጥ ማስገባት የተማሪዎቹን ደረጃ እና ባህላዊ ዳራቸውን፤ እና

f) የመድብለ ቋንቋ ተማሪዎች አካዴሚያዊ ስኬት ተማሪዎቹ፣ሁሉም አስተማሪዎች፣ቤተሰብ እና ማህበረሰቡ የሚጋሩት ኃላፊነት መሆኑን እውቅና መስጠት።

2. እንግሊዘኛ ቋንቋ የማዳበር (ELD) ፕሮግራም

a) እያንዳንዱ ትምህርት ቤት ከትምህርት ቤት ድጋፍ እና ደህንነት/የስርአተ ትምህርት እና የትምህርት መርሃ ግብሮች ቢሮ ጋር በመተባበር ብቁ ለሆኑ የመድብለ ቋንቋ ተማሪዎችን የተለያዩ ፍላጎቶች ምላሽ የሚሰጥ ELD ፕሮግራም ይሰጣል። ELD በአራቱ የቋንቋ ዘርፎች ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብ እና የእንግሊዝኛ አካዳሚክስ እና ማህበራዊ ቋንቋን መጠቀም እንዲችሉ ብቁ ለሆኑ የመድብለ ቋንቋ ተማሪዎች የተዘጋጀ ልዩ የትምህርት ፕሮግራም ነው።

b) ELD ሥርዓተ ትምህርት/ከሪኩለም –

(1) በጥናት ላይ የተመሰረተ፣

(2) ለእድሜ ተመጣጣኝ የሆነ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታ ደረጃዎችን በመጠበቅ የተነደፈ፣

(3) MSDE የእንግሊዝኛ ቋንቋ ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ ካሉ የብቃት ደረጃዎች ጋር የተጣጣመ፣

(4) ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የንባብ/እንግሊዘኛ/የቋንቋ ስነጥበብ ሥርዓተ ትምህርት የማንበብ እና የመጻፍ ዓላማዎች ጋር የተጣጣመ፤

(5) በመድብለ ቋንቋ ተማሪዎች የሚወክሉትን በርካታ የባህል እና የቋንቋ ዳራዎች የሚያንፀባርቅ፤ እና

(6) ተማሪዎች በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ትምህርት ሲከታተሉ ለሚገጥሟቸው የማስተማር ስልቶች እና የትምህርት ይዘቶች የሚያዘጋጃቸውን ትምህርት በመጠቀም ያስተምራል።

c) ተዛማጅ ELD አገልግሎቶች

(1) ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ቦርድ ፖሊሲ ABC፣ የቤተሰብ እና የትምህርት ቤት ትብብር ጋር በሚስማማ መልኩ፣ MCPS ስለ ተማሪ ትምህርት እና እድገት በርካታ ስልታዊ በሆነ መንገድ የሚተገበሩ ስልቶች እና መሳሪያዎችን በመጠቀም መደበኛ፣ ትርጉም ያለው የሁለትዮሽ ግንኙነት ያደርጋል፣ ይህም ወላጆች/አሳዳጊዎች እያደገ የመጣ የብዝሃ ቋንቋ ተማሪዎቻቸው ጥብቅ ትምህርት እና ትምህርታዊ እድሎችን እንዲያገኙ ስለሚያስፈልጉት ወሳኝ መመዘኛዎች፣ የኮርስ ቅደም ተከተሎች፣ የተማሪ አገልግሎት ትምህርት መስፈርቶች እና እድሎች፣ የጊዜ ሰሌዳዎች እና የማመልከት ሂደቶችን እንዲማሩ እድል ይሰጣቸዋል።

(2) ቋንቋን የሚመለከት የሕክምና ዘርፍ ካውንስለሮች (Language therapeutic counselors) ELD ፕሮግራም ላይ የተመዘገቡ ተማሪዎችን ለመርዳት እንደአግባቡ ለተማሪዎች የምክር አገልግሎት ይሰጣሉ።

(3) MCPS የአካል ጉዳተኝነት እንዳላቸው ለሚጠረጠሩ የብዝሃ ቋንቋ ተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋ ምዘና ጭምር፣የባህል እና የቋንቋ አድሎአዊነትን ለማስወገድ ሲያስፈልግ ግምገማዎችን ያካሄዳል።

d ለጀማሪ የመድብለ ቋንቋ ተማሪዎች የመማር-ማስተማር ፍላጎቶችን ለማሟላት የሰራተኞች የሙያ እድገት እና ጥራት የ ELD ፕሮግራም ዋና አካል ነው። የሙያ ማዳበር ትምህርት እድሎች ለሁሉም

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች ከጀማሪ የመድብለ ቋንቋ ተማሪዎች ጋር ክፍል ውስጥ ለሚሰሩ እና ለትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ይሰጣል።

3 መለየት እና እንደገና መመደብ

a) የቋንቋ ምዘና ለ ELD ፕሮግራም ብቁ የሆኑ ጀማሪ የመድብለ ቋንቋ ተማሪዎችን በመለየት የእንግሊዝኛ ቋንቋ የብቃት ደረጃቸውን በሚከተለው መልኩ ይወስናል፦

(1) የእንግሊዘኛ ቋንቋ የብቃት ምዘና የሚካሄደው ብቃት ባላቸው እና በሰለጠኑ ገምጋሚዎች ነው።

(2) ምዘናው የሚካሄደው MCPS ውስጥ መጀመሪያ በተመዘገቡበት ጊዜ በሜሪላንድ ቤት ውስጥ የሚጠቀሙበት ቋንቋ ዳሰሳ (HLS) ላይ ከሶስቱ ጥያቄዎች ሁለቱን ለሚመልሱ ተማሪዎች ሁሉ ነው።

b) ELD ፕሮግራም ውስጥ የሚሳተፉ ተማሪዎች MSDE መመሪያ ላይ የተቀመጡትን መመዘኛዎች ሲያሟሉ የእንግሊዘኛ ብቃት ያላቸው እና በድጋሚ የተመደቡ ጀማሪ መድብለ ቋንቋ ተናጋሪዎች ተብለው ይመደባሉ።

c) ከ ELD ፕሮግራም የወጡ ተማሪዎች አፈጻጸም በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት የእንግሊዝኛ ቋንቋ ማዳበር ቡድን ክትትል ይደረጋል፣ እና ለሁለት ዓመታት ተገቢው ድጋፍ ይሰጣል።

d) MSDE ባስቀመጠው መመሪያ መሰረት እንደ አስፈላጊነቱ በየጊዜው የመለየት እና የፕሮግራም ማጠናቀቂያ ሂደቶች ይከለሳሉ እና ይገመገማሉ።

D. ተፈላጊ ውጤት

1. ELD ፕሮግራም አገልግሎቶች ለሁሉም ብቁ ለሆኑ ጀማሪ የመድብለ ቋንቋ ተማሪዎች የሚሰጥ ሲሆን የተማሪዎቹ ዳራ እና የእንግሊዝኛ ቋንቋ የብቃት ደረጃዎችን ለማስተናገድ የተነደፉ ይሆናሉ።

2. ELD ፕሮግራም ውስጥ ከሚሳተፉ ተማሪዎች የሚጠበቀው የስኬት ደረጃ MCPS ውስጥ ካሉት ሁሉም ተማሪዎች ከሚጠበቀው የስኬት ደረጃ ጋር እኩል ተመጣጣኝ ነው።

3. ቋንቋ የጀማሪ መድብለ ቋንቋ ተማሪዎችን የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች ሁሉም ያላቸውን ከፍተኛ ጥራት ያለው የትምህርት እድሎችን እንዳያገኙ እንቅፋት መሆን የለበትም።

4. ትምህርት ተማሪዎች በተቻለ ፍጥነት እንግሊዘኛ እንዲማሩ ያስችላቸዋል፣ በተመሳሳይ በትምህርት ይዘት ከክፍል ደረጃ እኩዮቻቸው ወደ ኋላ እንዳይቀሩ ይረዳቸዋል።

5. MCPS ጀማሪ የመድብለ ቋንቋ ተማሪዎችን ብዝሃ ቋንቋ ተናጋሪነት እና የሌሎች ቋንቋዎችን ሊተርሲ፣ እንዲሁም ጀማሪ የመድብለ ቋንቋ ተማሪዎች ለትምህርት ክፍል እና ለትምህርት ቤት ማህበረሰብ የሚያመጡትን የቋንቋ እና የባህል እሴቶችን ትልቅ ዋጋ ይሰጣል።

E. የአተገባበር ስልቶች

የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት –

1. MCPS ውስጥ ጀማሪ የብዝሃ ቋንቋ ተማሪዎች ተገቢ ፕሮግራሞችን ለማዘጋጀት፣ ለመገምገም እና ለማሻሻል ጠቃሚ አሠራሮችን ያዳብራል፤

2. በሠነድ ለሚቀርቡት ፍላጎቶችን ባለው የበጀት አቅም መሠረት ሰራተኞችን እና የቁሳቁስ መገልገያዎችን/ሪሶርሶችን በየዓመቱ ይመድባል፣

3. ይህንን ፖሊሲ ተግባራዊ ለማድረግ ተገቢ የሆነ የገንዘብ ድጋፍ ከፌዴራል ለማግኘት ያመልክታል፤እና
4. ጀማሪ የመድብለ ቋንቋ ተናጋሪዎች እና ቤተሰቦቻቸው የሚያስፈልጋቸውን መርጃዎች ለማመቻቸት ከካውንቲ ኤጀንሲዎች እና የማህበረሰብ ድርጅቶች ጋር ይተባበራል።

F. ግምገማ እና ሪፖርት ማድረግ

1. በየዓመቱ፣የ ELD ፕሮግራም ተሳታፊዎች አካዴሚያዊ ግስጋሴ ለሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ በዓመታዊ ዘገባ ሪፖርት ይደረጋል።

2. MCPS ወቅታዊውን እና የበፊቱን ELD ፕሮግራም ተሳታፊዎችን በሚመለከት ሁሉንም የፌደራል እና የስቴት ሪፖርት ማቅረቢያ መስፈርቶችን ያሟላል።

3. ይህ ፖሊሲ በትምህርት ቦርድ ፖሊሲ የግምገማ ሂደት መሰረት ይገመገማል።

የፖሊሲው ዳራ፡- የውሳኔ ቁ. 77-80 ነው። ጃኑዋሪ 21 ቀን 1980 በውሳኔ ቁጥር 333-86፣ ጁን 12 ቀን 1986 ተሻሽሏል፣ በውሳኔ ቁጥር 599-99፣ኦክቶበር 14 ቀን 1999 ዓ.ም ተሻሽሏል፣ የወቅቱ የቢሮ ስያሜ ጁን 1, 2000 በውሳኔ ቁጥር 450-11 ሴፕቴምበር 13 ቀን 2011 ተሻሽሏል።